# አዳምን በስሱ

የአስካለች ልጅ አንዋር

**እውነት**

አዳም ማህበሩን የሚተች አይነት ደራሲ ነው። ይኽንንም ደጋግሞ ስራዎቹ ላይ አንፀባርቋል። በተለይም የልጅ አስተዳደጋችን ላይና በልጅነት ያለ ዓቅማችን ተጋላጭ የምንሆንባቸው እንዲሁም የሚሰጡን እውነቶች ምን ያህል ማንነታችንን እንደሚፈታተኑና እኛ ዉስጥ ለሚፈጠረው እያንዳንዱ የዛሬ ማንነት የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ያሳየናል።

ለማሳያ ‘አለንጋና ምስር’ ላይ ‘ዘላን’ የሚለው ተረኩ ላይ የሚገኘውን ተማሪው ልጅ እንዴት እንደሚሳደድ፤ ተባብረው የሚያሳድዱትም ታላላቆቹ ማለትም እሱ ልዩ ቦታን የሚሰጣቸው ሰዎች መሆናቸው ይኽንንም የሚያደርጉት የሰሩትንና እየሰሩት ያሉትን መልካም ያልሆነ ምግባር መሸፈኛነት እንደሆነ ያሳየናል። እዚህ ላይ ደግሞ ዉበትንም ኪነትንም አጣምሮ ማሳየቱን መመስከር ይቻላል።

‘ከሰማይ የወረደ ፍርፍር’ ላይ ‘ትርንጎና ገብረጉንዳን’ የሚለው ታሪኩን እንምዘዝ

ጩጬው በለጋ ዕድሜው አጉል ለሆነ የወሲብ ዓለም ተጋላጭ እንዲሆን ትርንጎ ታደርገዋለች።

ህፃናት ፊት የማይወሩ ተብሎ እየተሸሸጉ ከተያዙ እውነቶች ጋር አጉል ታገናኘዋለች። አልፎም እጅግ ትልቅ ቦታን ከሚሰጣቸው ቄስ ጋር ተኝታ እውስጡ ያቀረውን ዕምነት የሌለ ንዳ አፈር ድሜ ታስግጠዋለች። (ትርንጎና ገብረ ጉንዳን በጣም ከምወዳቸውና የተለየ ቦታ ካለኝ ታሪኮች አንዱ ነው። እርግጥ ሁሉንም ታሪኮቹን እወድለታለሁ) ከፀናሁም ት.ና ገ.ጉ ላይ የጀመርኩትን ትንታኔ (text interpretation) ጨርሼ እዚሁ ላይ እለጥፈው ይሆናል።

በተደጋጋሚ ተረኮቹ ላይ የሚያነሳቸው ሃሳቦች ልጆችን ዉሸት እየሞላን ነው እያሳደግናቸው ያለነው ዓይነት ነው።

አብዛኛውን ቦታ ላይ የሚዋሹ ታላላቆች፣ አንዱን ችግር ለማለፍ ሌላ ለችግር የሚያጋልጥ መንገድን የሙጥኝ ያሉ ታላላቆችን፤ ቂመኛ የሆኑ ታላላቆችን፤ ሃሜተኛ የሆኑ ታላላቆችን ያሳየናል። እነኚህም ሰዎች ተንኮሎቻቸው የሚጋለጠው በልጆች አማካኝነት ነው “ህፃናት ንፁህ ናቸው” የሚለውን ጥቅስ በደንብ የተጠቀመበትም ይመስለኛል።

አንዳንዴ ህፃናቱ እንዲህም ያስባሉ እያለንም ይመስለኛል። ደግሞም ህፃናት ጠያቂ ዓዕምሮ ነውና ያላቸው ዕምነታቸው ሲናድ፣ ዉሸትን ሲሰሙ ሌላም ሌላም “ለምን?” ማለታቸው የሚጠበቅ ይመስለኛል።

‘እብዱ ሺበሺን’ ደግሞ ላስታውስ ሺበሺ የሚገርም እብድ ነው። አሳሳሉን ምን ዓይነት አስፈሪ ግርማ ሞገስ አጎናፅፎ እንደሳለው እናስታውሳለን። ልጆች እያሳደዱ በድንጋይ የሚመቱትና እየሰደቡ የሚያበሳጩት። ሆኖም ምን አደረገ ያንን የጓጉበትን የብር ቀለበት ሲሰርቀው ደርሶበት ህፃኑ ዓይኖቹ እየተቁለጨለጩ ካሁን አሁን

በላኝ እያለ ሲጠባበቅ እናንተ እኮ ንፁህ ናችሁ፡ አዋቂዎች ናቸው የሚያበላሿችሁ ብሎ ፈትቶ ሰጥቶ አሰናበተው።

አለ ደግሞ እቴ ሜቴ ጋ አባቱን ልቡን አሻከረው እውነቱን ጠምዝዘውበት እንዴት እንዳሰናከሉት ያሳየናል። ብሎም እናቱ የከፋታችንን የመጠላለፋችንን ልክ "ሂትለር ሂትለር ይላሉ፣ ሂትለር ምን በደለኝ እዚህ አገሬ ከፋት አንሶኝ ነው ባህር 'ምሻገረው እያለች ሙሶሎኒ አባትህን መች ገደለው. . . "እያለች ብዙ ብዙ እያንዳንዱ ታሪኮቹ ላይ እነኚህን social critics(የማህበረሰብ ትችት) አላጣም።

Collective society (ማህበርተኛነት የአኗኗር ዘይቤ) የሚከተል ማህበረሰብ ዉስጥ የዕለት ተ'ለት ግንኙነቱ (interactions) የጠነከረ ሰለሚሆን ለግጭትም ሆነ መሰል ችግሮች ተጋላጭነታችን የሚሰፉ ይመስለኛል። እንደው ለማሳያነት ጠቃቀስኩ እንጂ ብዙ ብዙ ጉዳዮችን ይነካካል። የአካባቢ መራቆትን፣ ጥሬ ስጋ መውደዳችንና ተከትሎ የሚመጣ ችግር፣. . .

**ዉበትና ኪን**

እዚህ ላይ ብዙ ማለት በቻልኩ እወድ ነበረ፤ ደግሞም የኪኑ ዉበት አንዱን ስነካ ሌላ እየተመዘዘ እንደሚበዛብኝም ይታየኛል ሆኖም አንድ ሁለት ማሳያ ነገሮችን ብቻ አንስቼ ላልፍ ነው። ሌላውን ለሌላ ትቼና ለሌላ ጊዜም ጭምር ደግሞም "ለብልህ. . ." ነገር ነው።

አዳም (descriptive writer) ገላጭ ድርሰት የሚባለውን መንገድ የሚከተል ደራሲ ነው ከስራዎቹ እንደምንረዳው። የአንድ descriptive writer quality ተብለው ከሚጠቀሱት ጉዳዮች መሃከል ደግሞ እያንዳንዱን ጥቃቅን ጉዳይን የማተኮር ችሎታ ነው። ይንን ደግሞ የአዳም ድርሰቶች ላይ ሙሉ በሙሉ የምናገኘው ነው።

የሚገርመኝ እያንዳንዱን ጉዳይ ሲዘረዝር የሚገልፅበት መንገድ ትኩስ ነው። ያረጀ ነገር እንኳ ሲናገር በአዲስ መንገድ ነው።

ሌላው የቋንቋ ዉበቱ። በሚገርመኝ መጠን ልክ እንደገጣሚ ለቃላት ሲጠበብ አየዋለሁ። ቃላቱ በዝርው የተፃፉ ግጥሞች ጭምር ይመስሉኛል። ባለኝ እጅግ ጥቂት ንባብ አማርኛ ላይ እንዲህ በልቦለድ አይነት መጠበብን ሲጠበብ ማንንም አላስተዋልሁም።

ምንን እንዴት ማለት እንዳለበት የተረዳ ሰው እንደሆነ ነው የሚታየኝ።

ሁሌም የተለየ ዓይነት መንገድ መከተልን ይወዳል። ይኸም ማለት የልቦለድ ቅርፆቹ ላይ እንኳ ባለፈው የተጠቀመበትን መንገድ ይዞ በመመላለስ አያሰለችም።

ዕውነታንም ተከትሎ ሆነ ፋንታሲ ሲፅፍ የማሳመን ዓቅሙ ይገርመኛል። 'ዱለት፣ ጎሮና ጎሬ' የሚለው ተረኩ ላይ እናትዬዋ ወደ ዶሮነት ስትለወጥ ዉሸት ቢሆን እንኳ ዉሸቱ ላይ ሳይሆን የታሪኩ ፍሰት ላይ እንድጠመድ ነው ያደረገኝ። 'የብሩክታይት ጠጠርንም' ማስታወስ ይቻላል።

‘ህማማትና በገና’ ላይ ‘ትይዩ’ን በማንበብ ምን ያኽል ለሚልበት መንገድ እንደሚጠበብ ልብ ማለት ይቻላል አንድ ገፅ ላይ ሁለት ትዕይንትን ለማሳየት በጥቁርና ነጭ መደብ ላይ በመፃፍ የተጠቀመው መንገድ እንዴት አያስገርመኝ?

‘አለንጋና ምስር’ ላይ ‘እግርና ዜጋ’ እያለ በዲያግራም የሰራው ስራም ሚገርም ነው። ‘ሐምራዊ ሳቅ’፣. . . አሉ እንጂ ሰባቱ መንገዶች፣ ማንነታችን ከምናድግበት አካባቢና ከየዙረታችን ጋር የጊዜ መንፈስንም እንዴት እንደሚተሳሰር የሚያሳዩ

መዝገቡ የነኚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ጉዳዮች ሁሉ ስብስብ ዉጤት ነው። የተገፋ፣ መገፋቱን ለመሸሽ ጉብታዋን የሙጥኝ ያለ። ተገልሏል የተገለለውም በእንጀራ እናቱ እ.እ እያለ በምህፃረ ቃል የሚጠራት፤ በእህቱ (በሚደረግላት እንክብካቤ ሳቢያ የማትመቸው ዓይነት) ገመናዋን ለተደራሲያን የሚዘከዝከው።

በተረፈ መዝገቡ የአብዛኛው ልጅ ፊት ይዞ የተፈጠረ ህፃን እንደሆነ ይታየኛል።

መገፋትን ገና በጨቅላነቱ ያጣጣመ በዚህም የዓለም ሃቅ እንድትጣረስበት የሆነ።

በህጻንና የዋህ ዓይን ምንነታችንን የሚያሳይ በተምሳሌትነት የተሳለ ገ.ባህርይ እንደሆነ ነው የሚሰማኝ።
ይኽ እንግዲህ ከትውስታዬ ዉስጥ የቆነጠርሁትና ስለ አዳም በተለያዩ ጊዜያት የተጠራቀሙ ጉዳዮች ናቸው።

መልካም ጊዜ!